# የፌደራል ይቅርታ ቦርድ አባላት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓትና የአሠራር መመሪያ

179/2013

ሰኔ /2007 ዓ.ም.

| ተ. ቁ. | አርዕስት | ገጽ |
|---|---|---|
| | **ክፍል አንድ**<br>**ጠቅላላ** | |
| 1 | አጭር ርዕስ | 1 |
| 2 | ትርጓሜ | 2 |
| 3 | የፆታ አገላለጽ | 2 |
| 4 | የመመሪያው ዓላማ | 2 |
| 5 | የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን | 2 |
| | **ክፍል ሁለት** | |
| 6 | የቦርድ ስብሰባዎች | 3 |
| 7 | የቦርድ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር | 3 |
| 8 | የቦርድ ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት | 3 |
| 9 | የይቅርታ ጥያቄዎችን ስለመመርመር | 4 |
| 10 | ለውሳኔ ሃሳብ አቀራረብ የሚያገለግሉ መስፈርቶች | 5 |
| 11 | የይቅርታ ጥያቄ በልዩ ትኩረት ታይቶ የሚሰጥባቸው የወንጀል ዓይነቶች | 6 |
| 12 | ኃላፊነትን በአግባቡ ስለመወጣት | 6 |
| 13 | ከስብሰባው ራስን ስለማግለል | 7 |
| 14 | አግባብ ያልሆኑ ግንኙነቶች | 7 |
| 15 | በግል መረጃና ማስረጃ መቀበል የተከለከለ ስለመሆኑ | 7 |
| 16 | መመሪያውን ስለማሻሻል | 7 |
| 17 | መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ | 7-8 |

# የይቅርታ ቦርድ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት እና የአሰራር መመሪያ ቁጥር__1__

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት በሕግ መሠረት ይቅርታ እንደሚያደርግ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 71/7/ የተደነገገ በመሆኑ፤

የይቅርታ አሰጣጥ አፈፃፀም ሥነሥርዓት አዋጅ ቁጥር 395/1996 መሠረት ሲሰራበት የነበረውን የበለጠ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ ሲሰራበት የቆየው የህግ አፈጻጸም ወቅት የተገኙ ልምዶችን መሠረት በማድረግ አዋጅ ቁጥር 840/2006 በመደንገጉ እና፤

ለይቅርታ ቦርድ የሚቀርቡትን የይቅርታ ጥያቄዎች በተፋጠነ መልኩ ለማስተናገድ ይቻል ዘንድ የይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻዎች አሟልተው መያዝ የሚገባቸውን መረጃዎች ለአመልካቾች ከወዲሁ በግልጽ ማሳወቅ ፣ ታራሚዎችን የሚመለከት አስተያየት፣መረጃና ምስክርነት ከሚሰጡ ተቋማትና ግለሰቦች የሚፈለገውን ዝርዝር መረጃ በቅድሚያ ማሳወቅ እና የቦርድ አባላትም አዋጁን በአግባቡ ለማስፈፀም የሚያስችላቸውን ሥርዓት መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የይቅርታ ቦርድ ይህን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ በይቅርታ ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 840/2006 አንቀጽ 28/2/ መሠረት አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “ የተሻሻለው የይቅርታ ቦርድ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር179/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

2.1. “አዋጅ” ማለት የይቅርታ አሰጣጥና አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 840/2006 ነው፤

2.2. “ቦርድ” ማለት በአዋጁ አንቀጽ 6 መሠረት የተቋቋመ አካል ነው፤

2.3. " ቤተዘመድ"ማለት በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ህግ መሠረት የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ነው፣

2.4. "ጽ/ቤት" ማለት በፍትህ ሚኒስቴር ስር የሚተደደር የይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ነው፡፡

2.5. " መንግሥት"ማለት የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት ነው፡፡

2.6. "ይቅርታ ጥያቄ" ማለት በአዋጁ አንቀፅ 15፣ 16 እና 17 መሠረት የሚቀርብ ጥያቄ ነው፣

2.7 " ይቅርታ መስፈርት "ማለት በአዋጅቁጥር 840/2006 አንቀጽ 9/1/ " ለ " መሠረት የይቅርታ ቦርድ የሚያወጣው መስፈርት ነው፤

2.8. "ይቅርታ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀፅ 1 ላይ እንደተመለከተው አንድ ፍርድበሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣት ፍርዱ አፈፃፀምና ዓይነትበቀላል ሁኔታ እንዲፈፀም ማድረግ ነው፡፡

## 3. የፆታ አገላለፅ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

የህዝብ፣ የመንግስትና የታራሚዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል ታራሚዎች በፈፀሙት የወንጀል ድርጊትና ጥፋት የተፀፀቱና የታረሙ መሆኑን በማረጋገጥ ከማረሚያ ቤት ወጥተው ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው አምራችና ህግ አክባሪ ዜጋ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

## 5. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌደራል ፍርድ ቤቶች፣ በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች እንዲሁም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78/2/ መሰረት የፌደራል ጉዳዮችን የሚያስተናግዱ የክልል ፍርድ ቤቶች በሰጧቸው የመጨረሻ ውሳኔ በወንጀል ተፈርዶባቸው በፌዴራልና በክልል ማረሚያ ቤቶች በሚገኙ የፌዴራል ታራሚዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

### 6. የቦርዱ ስብሰባዎች

1.ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡

2. ቦርዱ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

3. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

4.የቦርዱ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ያለፋል፡ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡

### 7. የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 840/2006 አንቀጽ 10 ላይ የተመለከተው፤

1. የቦርዱን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት መምራት፣

2. በቦርዱ ጽህፈት ቤት በኩል ይቅርታ የተደረገላቸው ሰዎችን በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት የመግለጽ፡

3. ስለቦርዱ የሥራ አፈፃፀም በየስድስት ወሩ ለፕሬዚዳንቱ ሪፖርት ማቅረብ፡

4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይቅርታን አስመልክቶ የሚሰጡ ውሳኔዎች በመገናኛ ብዙሀን እንዲገለፁ ማድረግ፡ እና

5. በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡት ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት የማከናወን፡፡

### 8. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

የይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ሀላፊ ተግባርና ኃላፊነት በአዋጁ አንቀጽ 14 ላይ የተመለከተው ሆኖ በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡

8.1. የአዋጁ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጽ/ቤቱ ባዘጋጃቸው ቅፃ ቅጾች መሠረት ተገቢው ዝርዝር መረጃና ማረጋገጫ ያልተሰጠበትን ማመልከቻ መርምሮ ጉድለቱን በመለየት ተፈላጊው መረጃ ተሟልቶ እንዲቀርብ ለሚመለከተው አካል ይመልሳል፣

8.2. ቦርዱ ለህዝብና ለመንግስት ጥቅም ሲባል ባወጣው ይቅርታ የሚከለከልባቸው የወንጀል ዓይነቶች መስፈርት የተዘረዘሩትን በማገናዘብ የይቅርታ ጥያቄ ከቀረበ ለቦርድ

ማቅረብ ሣያስፈልግ እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከተው አካል አስረድቶ ይመልሳል፡ሆኖም ቅሬታ ካለ በተዘጋጀ የማመልከቻ ፎርም ጽፎ ለቦርድ ሰብሳቢ ማቅረብ ይችላል፡፡

8.3. የይቅርታ ጥያቄን አስመልክቶ በፕሬዚዳንቱ የተሰጠውን ውሳኔ በወቅቱ ለአመልካቾች የሚያሣውቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በቦርድ አባላት ውሳኔ ውድቅ የተደረጉትንም እንደ አስፈላጊነቱ ሊያሣውቅ ይችላል፡፡

## 9. *የይቅርታ ጥያቄዎችን ስለመመርመር*

9.1. ቦርዱ የሚያየው በአዋጁ አንቀጽ 15፣16 እና 17 መሠረት ተሟልተው የሚቀርቡለትን ማመልከቻዎች ብቻ ሆኖ ያልተሟላ መረጃ ካለ ተሟልቶ እንዲቀርብ የቦርዱን ጽ/ቤት ያዛል፡፡

9.2. ታራሚው ወይም በታራሚው ስም የይቅርታ ጥያቄ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ለይቅርታ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችሉና ታራሚውን የሚመለከቱ መረጃዎች ለማግኘት ታስቦ የተዘጋጁትን ቅጾች በትክክል በመሙላት በቅጾቹ ላይ የተመለከቱትን መጠይቆች አስመልክቶ የተሰጡት መረጃዎች ዕውነት መሆናቸውን በፊርማው ማረጋገጥ አለበት፡፡

9.3. በቅጾቹ ላይ የተመለከቱትን መጠይቆች አስመልክቶ ተገቢው መረጃ ካልተሰጠ ወይም መረጃው ሐሰት ሆኖ ከተገኘ የይቅርታ ጥያቄው ወዲያውኑ ውድቅ ይደረጋል፤

9.4. በይቅርታ ጠያቂው ላይ የተሰጠው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ማስረጃዎች ከይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻው ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

9.5. በፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር፣ በክልል ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤቶች እና በፍትህ ሚኒስቴር ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ተጠንቶ በብዛት የሚቀርብ ይቅርታ ጥያቄ በሰንጠረዥ ሆኖ፤ሠንጠረዡም የታራሚውን ስም ከነአያት፣ የሚገኝበት ማረሚያ ቤት፣ ዜግነት፣እድሜ፣ፆታ የአካል ጉዳትና የጤንነት ሁኔታ፣ የወንጀሉ አይነት፣ ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት ፣ የፍርዱ ልክ፣ ማረሚያ ቤት የገባበት ቀን፣ ጠቅላላ በማረሚያ ቤት የቆየበት ጊዜ፣ እርቅ መፈፀም በሚገባ ወንጀል እርቅ መፈፀሙ፣ ወይም ለመታረቅ ጥረት አድርጎ ያልቻለበት አሣማኝ ምክንያት፣ መቀጮ መክፈሉ ወይም መክፈል የማይችል ከሆነ ድሃ ለመሆኑ ከማህበራዊ ፍ/ቤት ማረጋገጫ ማቅረቡ፣ እና የማረሚያ ቤት አስተያየት " በይቅርታ ቢፈታ እንደገፋለን የሚሉበትን ምክንያት ወይም አንደግፍም" የሚሉበትን ምክንያት በተገቢ ሁኔታ የያዘ መሆን አለበት፡፡

## 10. ለውሳኔ ሀሳብ አቀራረብ የሚያገለግሉ መስፈርቶች

ቦርዱ የሚያቀርበውን የውሳኔ ሀሳብ በሚመለከት በተወሰኑ መስፈርቶች ሳይገደብ እንደጉዳዩ ሁኔታና ባህሪ ተገቢ መስሎ የታየውን የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ ሥልጣን ያለው ቢሆንም በውሳኔው ሀሳብ አቀራረብ ረገድ የሚከተሉትን አጠቃላይ መስፈርቶች ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡

10.1. የይቅርታ ጠያቂውን የአደገኛነት ባህሪ፣

10.2. የወንጀሉ ክብደትና ታራሚው የታሠረበትን ጊዜ፣

10.3.ይቅርታ ጠያቂው በከባድ በሽታ ተይዞ ለመታረም አስቸጋሪ መሆኑ በህክምና ቦርድ ከተረጋገጠ በልዩ ሁኔታ ሊቀርብ ይችላል፡፡

10.4. ይቅርታ ጠያቂው እርቅ በሚጠይቅ ወንጀል የተፈረደበት ከሆነ ከተበዳይ ወይም ተጎጂ ቤተሰብ ጋር ዕርቅ መፈፀሙ ወይም ለመፈፀም ያደረገው ጥረት፣እና ይህንን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን ማረጋገጥ፣

10.5. የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የተፈረደበት ከሆነ የ12 ዓመት እሥራቱን ከፈፀመ በኋላ የይቅርታ ጥያቄን ማስተናገድ የሚቻል መሆኑን፣

10.6. ከላይ በንዑስ ቁጥር 10:5 ከተደነገገው ውጭ ሌላ ቀላል እሥራት ወይም ጽኑ እሥራት የተፈረደበት ከሆነ ከተፈረደበት የእሥር ጊዜ 1/3ኛውን በማረሚያ ቤት በመታነፅ የቆየ ከሆነ፣

10.7. የግዴታ ሥራ ቅጣት የተወሰነበት ከሆነ የግዴታ ሥራውን ከፈፀመ፣

10.8. ለህዝብና ለመንግስት ጥቅም ሲባል በልዩ ሁኔታ መታየት የሚገባቸው የይቅርታ ጥያቄዎች፣

## 11 .የይቅርታ ጥያቄ በልዩ ትኩረት ታይቶ የሚሰጥባቸው የወንጀል አይነቶች፡.

11.1 በልዩ ሁኔታ በመንግሥት ካልታመነበት በስተቀር ከዚህበታች የተመለከቱት የወንጀል አይነቶች ካላቸው የወንጀል ባሀሪና አደገኝነት አንጻር በልዩ ትኩረት ታይቶ
የዚህን መመሪያ አንቀጽ 4 ዓላማ ለመተግበር ሲባል የይቅርታ ይደረግ የውሳኔ ሀሳብ ሊቀርብባቸው የሚችለው እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት አግባብ ይሆናል፡፡

ሀ) ሙስና፤

ለ) ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርና ስደተኞችን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር

ሐ) ሽብርተኝነት፤

መ) በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት፤

ሠ) የሃሰት ገንዘብ መሥራት ወይም ማዘዋወር፣

ረ) አደገኛ እጽ ማምረት፣ ማዘዋወር፣ ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም፤

ሰ) በሴቶች ወይም በሕጻናት ላይ የሚፈጸም የአስገድዶ መድፈር እና ጠለፋ ወንጀል፤

ሸ) በመሰረተ ልማት አውታሮች ማለትም በመብራት፣ ውሀ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ በባቡር መስመሮች ፣ ድልድዮች ፣ግድቦች እና መሰል የመሰረተ-ልማት አዉታሮች ላይ የሚፈጸም ወንጀል፣

## 12. ኃላፊነትን በአግባቡ ስለመወጣት

12.1 ማንኛውም የቦርድ አባል ለቦርድ የቀረቡትን የይቅርታ ጥያቄዎች በሚመለከት የሚያቀርበው ሀሳብ ሚዛናዊነት ያልጐደለው መሆኑን፣ ተጨባጭ በሆነ ምክንያትና ማስረጃ ላይ የተመሠረተ መሆኑን፣ የግል ጥላቻንና ጥቅምን መሠረት ያላደረገ መሆኑንና ከአድልዎ የፀዳ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

12.2 ማንኛውም የቦርድ አባል ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ የተወሰነውን የስብሰባ ጥሪ አክብሮ በስብሰባው ላይ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡

12.3. ማንኛውም የቦርድ አባል የፕሬዚዳንቱ ወይም በቦርዱ ውሳኔ ለሚመለከተው ሰው እንዲነገር ወይም ለሕዝብ ይፋ እንዲደረግ ውሳኔ ከተሰጣቸው ጉዳዮች በስተቀር ቦርዱ የተነጋገረባቸውን የውሳኔ ሀሳቦችና በሥራቸው አጋጣሚ ያወቃቸውን የታራሚውንና የ

የቤተሰቡን የግል ሕይወት የሚመለከቱ ምስጢራዊ መረጃዎች በምስጢር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤

## 13. *ራስን ስለማግለል*

ማንኛውም የቦርድ አባል አንድን የይቅርታ ጥያቄ ለማየት ከጥቅሙ ጋር የሚጋጭ ጉዳይ ሲያጋጥመው ይህንኑን ለቦርዱ ሰብሳቢ በማሳወቅ ጉዳዩ ከሚታይባቸው የቦርድ ስብሰባዎች ራሱን ማግለል አለበት፡፡

## 14. *አግባብ ያልሆኑ ግንኙነቶች*

ማንኛውም የቦርድ አባል ከመደበኛው የቦርድ ስብሰባና አሠራር ውጭ ወይም ደግሞ ቦርዱ በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ከይቅርታ ጠያቂዎች ጋር ወይም ስለእነርሱ በመሆን ይቅርታ ከሚጠይቅ ከማንኛውም ሌላ ሰው ጋር በቦርዱ በመታየት ላይ ባሉ ጉዳዮችና ወደፊትም በሚታዩ ጉዳዮች በግል መነጋገር የለበትም፡፡

## 15. *በግል መረጃና ማስረጃ መቀበል የተከለከለ ስለመሆኑ*

ማንኛውም የቦርድ አባል በሕግና በቦርዱ የአሠራር ደንብ መሠረት መረጃ እንዲሰጡ ከተፈቀደላቸው ተቋማትና ግለሰቦች ውጭ በቦርዱ በመታየት ላይ ያሉትንና ወደፊትም የሚታዩ ጉዳዮችን በሚመለከት ከማንኛውም ተቋምና ግለሰብ መረጃ መቀበልና መስጠትም የለበትም፡፡

## 16. *መመሪያውን ስለማሻሻል*

ቦርዱ ተገቢ መስሎ በታየው በማንኛውም ጊዜ ይህን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት የአሰራር መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 17. *መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*

ይህ መመሪያ በቦርድ አባላት ተፈርሞ ከወጣበት ከ ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አቶ ጌታቸው አምባዬ

አቶ ልዑል ካህሳይ

አቶ መንግሥቱ ቱፋ

አቶ ሙሉጌታ ውለታው

ወ/ሮ ፍሬነሽ መኩሪያ

አቶ ረመዳን አሸናፊ

ዶ/ር ከበደ ወርቁ

አቶ መስፍን አበበ

ወ/ት አይናለም ደበበ

አቶ ብርሀኑ አበራ

ወ/ሮ አልማዝ አብርሃ

አቶ ሀይሌ አዳሮ